# የ Apple Health Coverage (የጤና ሽፋንዎን) ማሳደስ

የApple Health (Medicaid) ሽፋን የጤና ሽፋንን ለማስጠበቅ ይቻል ዘንድ በየአመቱ መታደስ አለበት። የርስዎን ወይም የቤተሰብ አባልዎን የጤና ሽፋን ማደስ ስለሚገባዎት ነው። የማሳደሻ ጊዜው አልፎበት ሊሆን ይችላል።

## ሽፋኑን እንዴት ማሳደስ ይችላሉ

ከሚከተሉት አንዱን የእድሳት አማራጭ ይጠቀሙ:

### በበይነ መረብ (ኦንላይን)
### www.wahealthplanfinder.org

- የ Washington Healthplanfinder ሂሳብ ካለዎት ይግቡ እና በፈጣን ማስገቢያ ስር "ማመልከቻዬን ማዘመን እና ሽፋን ማደስ" የሚለውን ይምረጡ
- የ Healthplanfinder ሂሳብ ከሌለዎት "አሁን ማመልከት" የሚለውን ይጫኑ፣ መረጃዎን ያስገቡ እና በፈጣን ማስገቢያ ስር "ማመልከቻዬን ማዘመን እና ሽፋን ማደስ" የሚለውን ይምረጡ

### WAPlanfinder የስልክ አፕሊኬሽን መጠቀም

- የ Healthplanfinder ሂሳብ ካለዎት ወይም አዲስ መፍጠር ከፈለጉ ሽፋን ለማደስ የ WAPlanfinder አፕሊኬሽን ይጠቀሙ
- አፕሊኬሽኑ App Store እና Google Play ላይ ይገኛል

### ለ Healthplanfinder (የደምበኛ ድጋፍ ማዕከል) ይደውሉ በ 1-855-923-4633

### በኢሜል ያገኙትን የሚታደሰውን ሰነድ ያዘምኑ እና ፈርመው ከስር የሚገኙትን አማራጮች በመጠቀም ይላኩ፡

- **ፖስታ ፡-** PO Box 946, Olympia, WA 98507
- **ፋክስ፡-** 1-855-867-4467
- **CSO:** በአካባቢዎ የ DSHS የማህበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤት ሎቢው ጋር በሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ያስገቡ፡ **www.dshs.wa.gov/office-locations**

የእድሳት ማመልከቻዎ ከታየ በኋላ እርስዎ ውይንም የቤተሰብዎ አባል ሽፋኑን አስጠብቆ መቀጠል ይችል እንደሆን የሚያስረዳ ማሳወቂያ ይላክሎታል። ቀጣይነት ላለው የጤና ሽፋን ተጠቃሚ መሆን መቻልዎን ለመወሰን እድሳቱን ማጠናቀቅ አለብዎ።

## የቀነ ገደቡ አልፎዎታል?

የማሳደሻ ቀነ ገደቡ አልፎብዎት እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል የ Apple Health ሽፋን ያጣ ከሆነ እድሳቱን ከቀረቡት ተመላሽ ማድረጊያ አማራጮች በአንዱ በመጠቀም ለማጠናቀቅ የ90 ቀናት ጊዜ ይኖርዎታል። ህጋዊ ከሆኑ የጤና ሽፋንዎ ሽፋን ካጡበት ቀን ጀምሮ ያለምን የጊዜ ክፍተት የሚቀጥል ይሆናል።

ለApple Health ሽፋን ተጠቃሚነት ብቁ ካልሆኑ ለሌላ ብቁ ለሆነ የክፍያ ገንዘቡ ላይ እርዳታ በሚሰጥ ወይም በማይሰጥ የጤና እቅድ ተጠቃሚነት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህ የጤና እቅዶች ውስጥ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት እንዳለ ለማወቅ እድሳቱን ማጠናቀቅ ይገባዎታል።

## ጥያቄ አለዎት?

የ Apple Health ሽፋንን በተመለከተ ጥያቄ ካልዎት እባክዎ ለጤና እንክብካቤ ባለስልጣኑ የጤና እርዳታ የደምበኛ አገልግሎት ማእከል በሚከተለው ያነጋግሩ፡

- **ስልክ ቁጥር፡-**: 1-800-562-3022
- **ደህንነቱ የተጠበቀ የድህረ-ገጽ ቅጽ:** **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/**



Washington State Health Care Authority